# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 247 ጥር 30 2005 ገጽ 1


ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህ የወያኔ የመተካካትና ወንጀለኛን በወንጀለኛ የመለዋወጥ ስልት ህዝብን ለማታለል፤ የስልጣን ዘመንን ለማራዘምና የትግልን አቅጣጫን ለማሳት ሆን ተብሎ የሚደረግ ሴራ መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ተረድቶ ከወዲሁ ትግሉን እንዲያፋፍም በአደራ ጭምር ያስጠነቅቃል። ስለሆነም ንቅናቄያችን አሁንም በንቃት በመከታተል የስርአት ለውጥ በሃገራችን ለማምጣት አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ማናቸውም የትግል ስልቶች በመጠቀም ህወሃት/ኢህአዴግን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የሚገነፍል ድስት የሚያበላሸዉ እራሱን ነዉ

ግንቦት 7 መግለጫ ጥር 30 2005 ዓ.ም

በአለፉት ሁለትና ሦስት አመታት ዘረኞቹ የደደቢት ተዋንያን በተከታታይ ለህዝብ ካሳዩት ድራማና የኢትዮጵያ ህዝብም አይቶ እንዳላየ ታዝቦ ካለፋቸዉ የወያኔ ጉዶች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ የህዝብ ትግል አቅጣጫ በቀየረና እምርታ በአሳየ ቁጥር የወያኔ ጀሌዎች ባልተባ ብዕራቸዉ እየጻፉና ባልተካነ ችሎታቸዉ እየከየኑ እንደቤት ዉስጥ እቃቸዉ በሚቆጣጠሩት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ለህዝብ የሚያቀርቡት ሰዉ ሰዉ የማይሸት የባዶ ድራማ ትርኢት ነዉ። ይህ ለዜጎች መብትና ነጻነት መከበር በህይወታቸዉ ቆርጠዉ የሚታገሉ የህዝብ ልጆችን በሽብርተኝነት እየፈረጀ በድራማ መልክ ተቀነባብሮ ለትግሉ ባለቤት ለሆነዉ የኢትዮጵያ ህዘብ የሚቀርበዉ ጥራዝ ነጠቅ ትርኢት ወያኔ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያለዉን ንቀት በግልጽ ከማሳየት ዉጭ ሌላ የሚፈይደዉ ነገር አለ ብለዉ የሚያምኑ ካሉ እንደ ወያኔ የህዝብን ታላቅነት የሳቱና ህዝብን የሚንቁ ኃይሎች ብቻ ናቸዉ። በእርግጥም ይህ ተደራሲዉን በዉል ለይቶ የማያዉቅ ድራማ በግልጽ የሚነግረን አንድ ነገር ቢኖር ሽብርተኛ ተብለዉ ፍርድ ቤት መቅረብ ያለባቸዉ ሰላማዊ ዜጎችን እያደኑ የሚያስሩት፤ የሚደበድቡትና የሚገድሉት ዘረኞቹ የወያኔ ባለስልጣኖች ብቻ መሆናቸዉን ነዉ።

የዛሬ ሁለት አመት ግንቦት ሰባትን፤ የኦሮሞ ነጻነት ግንባርንና አገር ቤት ሽንጣቸዉን ገትረዉ የሚታገሉትን እነ እስክንድር ነጋን፤ ርእዮት አለሙን፤ ኡብላና ሌሊሳን፤ በቀለ ገርባንና አንዱአለም አራጌን ሽብርተኞች ናቸዉ ብሎ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማሳመን "አኬልዳማ" የሚል የቂል ድራማ ሰርቶ ያሳቀን ወያኔ ዘንድሮ ደግሞ መብቴ ይከበር ብሎ ከአንድ አመት በላይ በሰላማዊ መንገድ የታገለዉን የኢትዮጵያን ሙስሊም ህብረተሰብ ከለየላቸዉ አሸባሪዎች ከአልቃይዳና ከአልሸባብ ጋር የሚያዛምድ ***"ጅሃዳዊ ሐረካት"*** የሚባል ድራማ አዘጋጅቶ ከሰሞኑ ለህዝብ አሳይቷል። ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን ሁለቱን ትልልቅና ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሐይማኖቶች ለማጣላት ሆን ተብሎ የተሰራዉን የወያኔ ድራማ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳቀራረቡ ሳይሆን በጥንቃቄ እንዲመለከተዉና የወየኔን ህዝብን የማጋጨትና አገር የማፍረስ ሴራ እንዲያከሽፍ በአደራ ጭምር ያስጠነቅቃል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ከፋፋዩ የወያኔ አገዛዝ ህዝብን ከመሪዎቹ ለመነጠል የጠነሰሰው ሴራ ከሸፈ፣ በብዙ መቶሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች በከፍተኛ ቁጣ ተቃውሞአቸውን ሲያሰሙ ዋሉ

በትናንትናው እለት በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ለታሰሩት የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴዎች አጋርነታቸውን በመግለጽ በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰሙ መዋላቸውን ዘጋቢያችን ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሰሞኑን የተላለፈውን "ጅሀዳዊ ሀረካት" ፊልም በመቃወም ድምጻቸውን ሲያሰሙ የዋሉት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን "መሪዎቻችን ይፈቱ! ዓላማችን ኢስላማዊ መንግስት ሳይሆን የሀይማኖት ነፃነታችንን ማግኘት ነው! ድምፃችን ይሰማ፣ በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የሚደርሰው ጥቃት ይቁም"የሚሉ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን የሚያወግዙ መፈክሮች ሲያሰሙ ውለዋል።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በዚሁ ጂሃዳዊ ሃረካት ተብየ ፊልሙ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችን መሪዎች በሽብርተኝነት በመወንጀሉ ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ መንገዶችን ያጥለቀለቀ ሲሆን የታሰሩት ኮሚቴ አባላት አሁንም ህጋዊ ወኪሎቻችን ናቸው ይህንም በማያሻማ ሁኔታ እናረጋግጣለን ማለታቸውን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጹአል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት በአንዋር መስጊድ የተገኘው ህዝብ በተለይም ቀደም ባሉት ጊዚያቶች በተለየ መልኩ በመሪዎቹ ላይ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ያደረሰው በደልና ግፍ እጅግ ያሳዘነውና ያስቆጣው መሆኑ በግልጽ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ዘራፊው የወያኔ አገዛዝ ለዓባይ ግድብ ቦንድ ግዥ በሚል የጠራው ስብሰባ ጥቃት ደረሰበት

ዘረኛውና ዘራፊው የወያኔ አገዛዝ ከአንድ ሳምንት በፊት ጀምሮ ያስያዘውና ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ቦንድ- ለማሰባሰብ ያለመበት ስብሰባ በሳውዲ ከሚኖሩት ኢትዮጵያዊያን በደረሰበት ከፍተኛ ተቃውሞ ሳይሳካ መቅረቱንና ስብሰባውን ለመምራት የተገኙት የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናትና ሆድ አደሮች አንገታቸውን ደፍተውና ተሸማቀው እንዲመለሱ ማስገደዱን ዘጋቢያችን ከስፍራው ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

በዚህ የቦንድ ማሰባሰቢያ ስብሰባ በሪያድና አካባቢው የሞኖሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ከወትሮው በተለዬ መልኩ በስፍራው ቀደም ብለው በመገኘት የኮሙኒቲውን አዳራሽ ከአፍ እስከ ገደፉ የሞሉት ሲሆን የቦንድ ግዥውን ፕሮግራም ለመምራት ወደዚያው ያቀኑት የኢህአዴግ ባለስልጣናትም በስብሰባው ከተገኘው በርካታ ሰው ደኅስ ያለ ገንዘብ እንደሚያሰባስቡ ተስፋ አድርገው እንደነበር ዘጋቢያችን ገልጹአል።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ የወያኔው አገዛዝ ሰሞኑን "ጂሀዳዊ ሀረካት" በሚል ርዕስ በለቀቀው ፊልም ላይ በእስር ላይ ያሉትን የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴዎች ላይ ባሰማው የፈጠራ ክስና ውንጀላ ምክንያት ኢትዮጵያዊያኑ ቁጣቸው በመቀጣጠሉ በአዳራሹ የተገኙት ሙስሊሞች የቦንድ ግዥውን ስብሰባ ወደ ከፍተኛ የተቃውሞ ትዕይንት የቀየሩት መሆኑ ታውቋኡአል።

"ግድቡ ከመሪዎቻችን መፈታትና ከሰላማችን በሁዋላ ይደርሳል" በማለት ቅሬታቸውን መግለጽ የጀመሩት በሪያድ የሚኖሩ ሙስሊሞች፤ "ኢቲቪ ሌባ! ኢቲቪ አሸባሪ! መጂሊስ ይውረድ! መሪዎቻችን ይፈቱ!ድምፃችን ይሰማ!" በማለት አዳራሹንና አካባቢውን በከፍተኛ ጩኸት አናውጠውታል።

በሳውዲ አረቢያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወያኔ በህዝበ ሙስሊሙ ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍ እና በደል በመቃወም ተደጋጋሚ የተቃውሞ ደብዳቤ ማስገባታቸው ይታወሳል።

## የወያኔ ጀሃዳዊ ሀረካት ድራማ የሙስሊሙን ማህበረሰብ ጥያቄ እንደማያዳፍነው ተገለጸ

ህዝብን ርስ በርስ በማጋጨትና በማዋጋት ራሱን በስልጣን ኮርቻ ኮፍሶ ለዘመናት መጉዋዝ የሚፈልገው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ ከትናንት በስቲያ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ እንደፈለገው በሚጫወትባቸው ሚዲያዎቹ ያስተላለፈው ጀሃዳዊ ሃረካት ድራማ በኢትዮፕያዊያን እየተጣጣለና እየተወገዘ መሆኑን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በሃገር ውስጥ በሰላማዊ ትግል እየተንቀሳቀሰ ያለው አንድነት ፓርቲ " በ‹‹ጀሃዳዊ ሃረካት›› ትረካ የሙስሊሙን ማህበረሰብ ጥያቄ ማዳፈን አይቻልም!" በሚል ርእስ መግለጫ፣ ማውጣቱ ታውቋአል። አንድነት በዚሁ መግለጫው በገዢው ፓርቲ ድርጊት ማፈሩንና ማዘኑን ገልጾ የከትናንት በስቲያ አዲስ ድራማው ገዥው ፓርቲ ዜጎች በማንኛውም መንገድ የሚያነሱትን ጥያቄ በግልጽና በውይይት መፍታት ያለመፈለጉ ግልጽ ሀገራዊ አደጋ እየሆነ መምጣቱ እየታየው ነው ብሉአል። በመቀጠልም "ኢትዮጵያን የምታክል ትልቅ ሀገር እያስተዳደረ ባለ አገዛዝ" ማዘኑን ገልጾ በኢትዮጵያ ሕዝብ ግብር የሚተዳደረው ነገር ግን የገዥው ፓርቲ መሳሪያ በመሆን የሕዝብ ጥያቄዎችን ለማፈን ተባባሪ መሳሪያ ሆኖ እያለገለ ያለው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ‹‹ጀሃዳዊ ሃረካት›› በሚል የተሰናዳና እንደተለመደው የሙስሊሙን ህዝብ ጥያቄን ለማዳፈን የተዘጋጀ አይነት ትረካ ሲያቀርብ የመጀመሪያው አለመሆኑን አስታውሷል።

በበረከት ስምኦንና በጓደኞቹ ተቀነባብሮ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሊቀርብ ሲል በፌደራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የታገደዉ "ጂሀዳዊ ሀረካት" የሚባል ፊልም እገዳዉ በተሰማ በሰአታት ውስጥ በወያኔ ባለስልጣኖች ግፊት ተነስቶ ፊልሙ በኢቲቪ የታየ መሆኑን በስፋት መዘገቡ ይታወሳል።

ኢቲቪ ያቀረበው ፊልም የኢትዮጵያን እስልምና እምነት መሪዎች ከአልሸባብና ከአልቃይዳ ጋር በአንድ ጎራ መድቦ የሚወነጅል ሲሆን በብዙዎች ግምት የፊልሙ ዋና አላማ ከአንድ ሺ አመት በላይ በሰላም ተከባብረዉ የኖሩትን ሁለቱን ትልልቅ የኢትዮጵያ ሀይማኖቶች እርስ በርስ እንዲጋጩ ለማድረግ መሆኑ እየተነገረ ይገኛል። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች እንደገለጹት ይህ የሙስሊሙንና የክርስቲያኑን ህብረተሰብ ለማጋጨት (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የጉልቻ መለዋወጥ...

አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ በዜጎች ላይ የሚደርሰዉ ጭቆናና ግፍ ከዕለት ወደ ዕለት እየከፋ መጥቶ ዛሬ "ባለራዕዩ" መሪ ህዝብ ላይ የጫነዉ መከራና መአት ወደ ራስ አልባው መሪ በፍጥነት እየተሸጋገረ የግፈኞች ስርዐት አገርንና ትዉልድን እያጠፉ ነዉ። ሻል ያለ ግዜ ይመጣል እያለ የወደፊቱን ብሩህ ዘመን የሚጠባበዉ የኢትዮጵያ ህዝብም ተስፋዉም ትዕግስቱም ተሟጥጠዉ የወያኔን አማራጭ ብቻ ሳይሆን ወያኔን የሚያስወግድበትን አማራጮች ጭምር እየፈለገ ነዉ።

የዘረኛው ወያኔ ስርአት ቁንጮ መለስ ዜናዊን ለይስሙላ የተካዉሃይለማርያም ደሳለኝ በአንድ በኩል የህዝብ መነሳሳት ለመገደብ በሌላ በኩል ደግሞ የራሱን ፍርሃት ለመሸፈን ሀገራችንን ድቅድቅ ጨለማ ዉስጥ በማስገባትና በወገናችን ላይ የሚያደርሰውን በደል አጠናክሮ በመቀጠል ኢትዮጵያውያን ስለ ብርሃን መውጣት እንዳያወሩ፣ እንዳያልሙ፤ ስለ ነገዉ የነጻነት ተስፋ እንዳይተነፍሱ፣ ስለ ነጻነት እንዳያዘምሩ ለማድረግ ልሳን ዘጊ የሆኑ የስርአቱ ጀሌዎችን በመምረጥ ሰቆቃው በከፋና በተጠናከረ መልኩ ህዝብና ሀገርን አውዳሚ የሆነ ሃይላቸውን በመጠቀም በንጹሃን ዜጎች ላይ ኢ-ሰበአዊ የሆነ አስነዋሪ ድርጊት እያስፈጸመ ነው።

የመለስ ዜናዊን ሥልጣን ሳይሆን ወንበር ብቻ የወረሰዉ ሃይለማርያም ደሳለኝ የራሱ ህሊና የሚያዝዘዉን ስራ መስራት ሲገባው የህወሃት አለቆቹን በመፍራትና የነሱን ቡራኬ ለማግኘት ሲል የኢትዮጵያን ህዝብ ለሰዉ በላ የህወሃት ባለስልጣኖች አሳልፎ እየሰጠ ነዉ። ይህ ነዉ እንግዲህ ከመለስ ዜናዊ ወደ ሃይለማርያም ደሳለኝ የተደረገው ሽግግር።

መላው የሀገራችን ህዝብ አዛውንቱ፣ ወጣቱ፣ ምሁሩ፣ ሰርቶ አደሩ ገበሬውና፣ ህጻናት ሳይቀሩ ዛሬ የወያኔ የስቃይ ሰለባ እና ገፈት ቀማሽ ያልሆነ ትውልድ ከቶ የለም።በከፍተኛ ተቋማት ተማሪዎችና አስተማሪዎች ላይ የሚደርሰው በደል፣ በእምነት ቦታዎች የሚሰማው እሮሮ፣ የማህበረሰባዊ ተቋማትን የማፍርስ አደጋ እና ሌሎችም እኩይ ተግባራት ተጨምረው የስርአቱን የግፍ በትር ያልቀመሰ ዜጋ የለምም።

ይህ የወያኔ ስርአት የጉልቻ መለዋወጥ ከትግላችን ለአንዲት ደቂቃም ቢሆን ሊያዘናጋን አይገባም፡፡ ችግሩን ከማግባባትና መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ ማፋፋምን፣ መጨቆንን የመረጠው የህወሃት/ኢህአዴግ ቡድን፤ በፍጹም ሊታመን የማይችል፤ ህዝባዊ ድጋፍ የሌለው፣ ብሄራዊ አንድነትን የማያውቅ፣ ሰበአዊነት የማይሰማው አካል በመሆኑ ዛሬ ልናስወግደው የሚገባ ዘረኛ ድርጅት ስለመሆኑ በአንድ ቋንቋ በቃህ ልንለው ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያችን የሚያስፈልጋት የሰው ለውጥ ሳይሆን ስር ነቀል የሆነ የስርአት ለውጥ ነው፤ ይህ ማለት ደግሞ ከአገራችን ዉስጥ ተነቅሎ መወገድ ያለበት ወያኔ/ኢህአዴግ እራሱ ነው። ሌላው ለውጥ ኢትዮጵያዊው ወጣት ከአበው የተማረውን፣ የወረሰውን አመኔታን በመገንባት የውርደት ዝምታን በእምቢተኝነት በመለወጥ የማያዳግም የስርአት ለውጥ እንዲመጣ አበክሮ በመታገል፤ ኢትዮጵያን ወደ ዘላቂ ሰላምና አንድነት ማምጣት ነው።

ከመለስ ዜናዊ ወደ ሃይለማርያም ደሳለኝ የተደረገው ሽግግር የአንድን ፓርቲ ቡድናዊና ግለሰባዊ ፍላጎትና ጥቅም ማእከል ያደረገ መሆኑ ዛሬ ለምናየዉና ተባብሶ ለቀጠለው አፈና፣ ግድያ፤ ቤተሰብ መፍረስ፤ የኑሮ መገሳቆልና በአጠቃላይ በ የነገ ተስፋው መጨለም ምክንያትሆኗል።

የወያኔ አገዛዝ "በመተካካት" ስም ህወሃት የበላይነቱን እንደያዘ የመቀጠል ህልም ያለው መሆኑን አረጋግጦልናል። ስለዚህ የፍትህ እጦት፤ የውሸት ምርጫዎች መብዛት፤ የሰብዓዊ መብቶች መረገጥ፤ የሥራ አጥነት መበራከት፣ የአግአዚ ጦር ሠራዊትና እና "የጆሮ ጠቢዎች" በወገናችን የሚያደርሱት እልቂትና ስቃይ ሰለባ የሆናችሁና ነጻነትና የአገራችሁ አንድነት የሚያንገበግባችሁ ዜጎች ሁሉ አሁን ወቅቱ የሚሻው የትግል ጊዜ ላይ በመሆናችን፤ የድል አጥቢያ አብሳሪ የሆኑ ወጣት የነጻነት ታጋዮችን በመቀላቀል ራሳችሁን፤ ወገናችሁንና አገራችሁን ታደጉ።

ግንቦት 7 የፍትህ፤የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህ የወያኔ የመተካካትና ወንጀለኛን በወንጀለኛ የመለዋወጥ ስልት ህዝብን ለማታለል፤ የስልጣን ዘመንን ለማራዘምና የትግልን አቅጣጫን ለማሳት ሆን ተብሎ የሚደረግ ሴራ መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ተረድቶ ከወዲሁ ትግሉን እንዲያፋፍም በአደራ ጭምር ያስጠነቅቃል። ስለሆነም ንቅናቄያችን አሁንም በንቃት በመከታተል የስርአት ለውጥ በሃገራችን ለማምጣት አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ማናቸውም የትግል ስልቶች በመጠቀም ህወሃት/ኢህአዴግን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## የሚገነፍል ድስት የሚያበላሸዉ እራሱን ነዉ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ኢትዮጵያ እስልምናንም ሆነ ክርስትናን በቅድምያ ከተቀበሉ አገሮች አንዷ መሆኗ ብቻ ሳይሆን ክርስትናና እስልምና ከአንድ ሺ አመታት በላይ በሠላም ተከባብረዉ ጎን ለጎን የኖሩባት ብቸኛ አገር ናት። የአገር አንድነትና የህዝብ ሠላም እረፍት የሚነሳዉ ወያኔ ግን ይህንን ዘመናት ያስቆጠረ ታሪክ ለመለወጥና የህዝብን በሠላም አብሮ መኖር ለማደፍረስ ቆርጦ የተነሳ ይመስላል። የኢትዮጵያ ህዝብ በሠላም ኖረም አልኖረ ወያኔ "ሠላም" የሚለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ እየተረገጠ አንገቱን ደፍቶ እስከተገዛለት ድረስ ብቻ ነዉ። ወያኔ ሰሞኑን **"ጅሃዳዊ ሐረካት"** የሚል ድራማ ሰርቶ ለህዝብ ማስተላለፍ የፈለገዉ መልዕክትም በሠላም መኖር ከፈለጋችሁ እኔ የምላችሁን ብቻ ስሙ ካለዚያ ጂሃዲስቶች እጅ ትወድቃላችሁ የሚል ነዉ። ግንቦት ሰባት ይህንን ቅንጣት ታክል ተአማኒነት የሌለዉ የወያኔ መልዕልት የሚሰማ ህሊና ያለዉ ኢትዮጵያዊ አለ ብሎ ባያምንም የተደጋጋመ ዉሸት አንዳንዴ እዉነት የመምሰል ዝንባሌ ስላለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ አይነቱ አደጋ እራሱን እንዲጠብቅ ከወዲሁ ያስጠነቅቃል። ወያኔ በተጨነቀ ቁጥር የቂሎች ድራማን መስራት ባህሪው ነው።

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የዛሬ ሁለት አመት **አኬልዳማን** አይቶ ትግሉን አጠናክሮ የቀጠለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬም ጅሃዳዊ ሐረካትን አይቶ የጀመረዉን ትግል ከፍጻሜዉ ለማድረስ በተጠንቀቅ እንዲቆም ወገናዊ ጥሪዉን ያለስተላልፋል። የዘረኞች ስርዓት ሙሉ ለሙሉ እስካልተደመሰሰ ድረስ ኢትዮጵያ ዉስጥ በተናጠል መብቱና ነጻነቱ የሚከበር የህብረተሰብ ክፍል የለምና የእስልምና እምነት ተከታዮች ጀመሩትን የመብትና የነጻነት ትግል የኢትዮጵያ ህዝብ እንደራሱ ትግል አድርጎ በማቀፍ እራሱን ከዘረኞችና ከዘራፊዎች ነጻ እንዲያወጣ ግንቦት ሰባት የትግል ጥሪዉን ያስተላልፋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## የወያኔ አቀንቃኝ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ የመለስ ዜናዊ ፎቶዎችና ፖስተሮች ይነሱ! ሲል ጠየቀ

ጋዜጣው በትናንትናው እለት ርዕሰ-አንቀጹ የመለስ ፎቶና ፖስተር ያልተሰቀለበትን የአዲስ አበባ ጎዳና ፈልጎ ማግኘት እንደማይቻልና ፎቷዎቹም በሁሉም ስፍራ እንዳለ በመጥቀስ፡- "አሁን ግን ይብቃ! ፎቶዎቹና ፖስተሮቹ ይነሱ!እንላለን" ሲል ጠይቋል።

ሪፖርተር "በፖስተሮቹና በፎቶግራፎቹ መሰቀል ለመነገድ፣ ለማስመሰልና ለማጭበርበር የሚፈልግ ሰው ካለም በቃህ ሊባል ይገባል፡፡ በመለስ ዜናዊ ስም አትነግድ፣ አታጭበርብር፣ አታታል ሊባል ይገባዋል" ብሏል። አስከትሎም፡- "በተግባር የማይደገፍ የፎቶና የፖስተር መለጣጠፍ መንፈስ ግን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። ሒደቱም በጊዜ ወሰን ውስጥ ሊከናወን ይገባል፡፡ በመሆኑም የዚህ ዓይነቱን ጨዋታ ይቁም፡ ፎቶዎች ይነሱ፡ ብሏል። በመጨረሻም ቃላትም ትርጉም ይኑራቸው፡፡ በቃላት ድርደራ ብቻ «ራዕይ» እና «ሌጋሲ» እያልን እየለፈለፍን በተግባር ግን ራዕዩንና ሌጋሲውን የሚፃረር ሥራ የምንሠራ ከሆነ ያስተዛዝባል፣ ብሉአል።

በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያዊያን የመለስ ዜናዊ ስሙ ሲጠራ እያንገሸገሻቸው መሆኑን በተለያዩ መንገዶች ሲገልጹ እየተስተዋለ ነው። ሰው ፎቶውን ማዬት ሰልችቷል፤ አንገሸግሾታል ወደዚያ አንሱልን" "እኔን የናፈቀኝ ቀጥሎ ደግሞ የማን እንደሚሰቀል ማወቅ ነው" ፣ ስለመለስ ዜናዊ መስማቱና ማየቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንገሸግሾታል እጅ እጅ ብሎታል ሀገር ጥሎ ቢጥፋ ደስ ይለዋል ፎቶዎቹን የሚቀዳድድባቸው ጊዜ እየናፈቀ ነው የሚሉት ከብዙዎቹ የተወሰዱ ናቸው።

# ሰሚ ያጣ ጩኸት

(ከኢትዮጵያ ከአንድ አድማጫችን ለዝግጅት ክፍላችን የደረስን)

ይድረስ ለሀገሬ ህዝብ እንዲሁም በመላው አለም ተበትናችሁ የኑሮን ውጣውረድ ለማሸነፍ ቀን ከሌሊት ለምትባዝኑ ወገኖቼ በቅድሞያ በአሩ አምላካችን እና ፈጣሪያችን በመድህኔአለም ፍቅር ሰላምታዬ ይድረሳችሁ። ከሁሉ አስቀድሜ የምነግራችሁ ሀገራችን ኢትዮጵያ በእግዚአብሄር ቸርነት፣ በአባቶቻችን ጸሎት እና እንዲሁም በጀግኖቻችን መስዋእትነት ነጻነቷን አስከብራ መኖሯ ሁላችሁም የምታውቁት ሀቅ በመሆኑ ስላለፈው ታሪክ በማውጋት ጊዜያችሁን መፍጀት አልሻም። ሆኖም ግን ያቺ ለዘመናት ነጻነቷን አስከብራ የኖረች ባለታሪክ ሀገር ዛሬ ይህ ትውልድ በህይወት ቆሞ አይኑ እያየ ታሪኳ ተሰርዞ፣ አንድነቷ ተሸርሽሮ፣ ዜጎቿ በዘረኞች ጥይት በረሃብና በበሽታ እያለቁ ዝም ማለት በምንኖርባት በዚህች ምድር ብቻ ሳይሆን በሰማያዊውአለምም የሚያስጠይቅ በመሆኑ ይህችን አንዲት ብጣሽ ወረቀት ለመጻፍ ተገደድኩ።

በመጽሀፍ ቅዱስ እንደተማርነው ጌታችን እና መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር ከመጣ በሁዋላ ጽድቅን እየሰበከ የሰው ልጆች ከሀጢያታቸው እንዲመለሱና ከክፉ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አስተምሮ በሁዋላም የሰው ልጅን ከሀጢያት ባርነት ነጻ ለማውጣት አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ሁሉን ማድረግ እየቻለ በመስቀል ላይ ውሎ ደሙን አፍስሶ፣ ስጋውን ቆርሶ የዲያብሎስን ስራና የሀጢያትን ባርነት በደሙ ከእኛ ከሰው ልጆች ላይ ማስወገዱ ተጠቅሷል። የዚህ ጽሁፍ ዋና አላማም ስለ ክርስትና እና ስለ መጽሀፍ ቅዱስ ለመስበክ ወይም ለማስተማር ሳይሆን የናዝሬቱ ኢየሱስ እኛን ልጆቹን ከዲያብሎስ ባርነት ለጻ ለማውጣት እሱ አምላክ ሆኖ ደሙን ካፈሰሰ ዛሬ በእግዚአብሄር ቤት ተሰብስበን የክርስቶስ ሀዋርያት ነን የምንል ጳጳሳት፣ ኤጲስቆጶሳት፣ ካህናት እና ዲያቆናት ዛሬ በምድራችን በኢትዮጵያ ህዝበ ምእመናኑ እና በአጠቃላይ ህዝባችን በዲያብሎስ የበኩር ልጆች መከራቸውን ሲያዩ፣ ሲገደሉ፣ ሲገረፉና ሲሰደዱ፣ አብያተ ክርስትያናት ሲቃጠሉ እና ሲፈርሱ፣ ቅዱሳን ገዳማት ሲደፈሩና የዘረኞች ካድሬዎች መጫወቻ ሲሆኑ፣ በአጠቃላይ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ታሪኳ ሲፋቅና ሲጠፋ፣ ደጋጎቹ አባቶች ጠብቀው ያቆዩት ንዋየ ቅድሳትና ቅዱሳን መጽሀፍት በአለም ገበያ ላይ ቀርበው ለባእዳን ሲቸረቸሩ፣ ዜጎቻችን በረሀብ እያለቁ መሬቷ ለባእዳን ሲቸበቸብ በአይናችን በብረቱ እያየን እንዳላየን፣ እየሰማን እንዳልሰማን ከሆንን ከዘረኞቹ ሀገር አጥፊ የዲያብሎስ ልጆች በምን ተለየን? እግዚአብሄር የሰው ልጆችን ከባርነት ለማዳን ልጁን ልኮ በደሙ ካዳነን እኛስ የክርስቶስ ሀዋርያት ነን የምንል ካህናቶች የወገኖቻችን ደም አይገደንምን? የወገኖቻችን ስቃይና ሰቆቃስ አይሰማንምን? እግዚአብሄር ፍቅር ነው! እግዚአብሄር እውነት ነው! እግዚአብሄር አያዳላም ታዲያ ዛሬ እኛስ በአይናችን በብረቱ የምናየውን ያለቅጥ ሞልቶ በመፍሰስ ላይ ያለውን ግፍ እንዳላየና እንዳልሰማ ስናልፈው እውነትን አልተፈታተናትምን? እግዚአብሄር በወንጌሉ አትግደል! አትስረቅ! በሀሰት አትመስክር ማለቱን እናውቃለን ታዲያ የምንዋሸው እራሳችንን ነው ወይስ እግዚአብሄርን? ይህ በምድር ላይ የምንኖረው ምድራዊ አለም ጊዜያዊና ሃላፊ ከንቱ እንደሆነ ይልቅስ መናፈቅ ያለብን ሰማያዊውን አለም እንደሆነ መጽሃፋን እየገለጥን የምንሰብክ ካህናቶችና አባቶች በተቃራኒው ለምድራዊው አለም ተሸንፈን፣ የዚህን አለም ገዢዎች ፈርተን እግዚአብሄር በአምሳሉ የፈጠረው ፍጥረት በዲያብሎስ ልጆች ሲሰቃይና ሲገደል እያየን አላየንም እየሰማን አልሰማንም ማለቱ ነገ በሰማያዊው አለም ለፍርድ ቀን ስንቀርብ የሚያሰጠይቀን እና ዋጋ የሚያስከፍለን መሆኑን በውል ልንገነዘበው ይገባል። በመሆኑም የእግዚአብሄር አገልጋይ የሆንን ካህናቶችና አባቶች ይህንን ምድራዊ አለም ንቀንና ተጠይፈን በሰማያዊው አለም የጽድቅን መንግስት ለመውረስ እንበቃ ዘንድ ዛሬ በሀገራችን በቅድስት ኢትዮጵያ ላይ እየተፈጸመ ያለውን መከራ፣ የህዝበ ምእመናኑን ለቅሶና ሮሮ እንዲሁም እግዚኦታ አዳምጠን ከወገኖቻችን ጋር ለነጻነታችን፣ ለሃይማኖታችን እና ለሀገራችን አንድነት ምንችለውንና እግዚአብሄር የወደደውን እንድናደርግ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

በመቀጠልም ኢትዮጵያዊ የሆንክ ወገኔ ሁሉ ክርስትያን፣ እስላም ወይም እምነት የለሽ ሳትል በዘር ሳትከፋፈል በአንድ ላይ በጋራ ተነስተህ ይህችን ታሪካዊት እና ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያን ለመታደግ እጅ ለጅ መያያዝ ይኖርበሃል። ባለፉት ዘመናት ደጋጎቹ አባቶቻችን ዘር ሳይለዩ በሃይማኖት ሳይከፋፈሉ አንድነታችንን ለመፈታተን በመጡ ጠላቶቻችን ላይ በጋራ በማበር ቀፎው እንደተነካበት ንብ ከአራቱም ማእዘናት ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምስራቅና ከምእራብ በመትመም ደማቸውን አፍስሰው፣ አጥንታቸውን፣ ከስክሰው በመርዝ ጪስ እየተቃጠሉ ጠላትን አደባይተውና አሳፍረው ወደመጣበት በመመለስ በደም የተጻፈ ታሪክ ትተውልን አልፈዋል። ዛሬም ይህ ኢትዮጵያዊ ትውልድ የአባቶቹ ልጅ በመሆኑ ሴት፣ ወንድ፣ እስላም፣ ክርስትያን ሳይል እግዚአብሄር ሲፈጥረን ያጎናጸፈንን ነጻነት የሚባል ጸጋ ለመቀዳጀትና ኢትዮጵያዊ አንድነቱን፣ በነጻ የማምለክ መብቱን ለማስከበር እጅ ለእጅ ተያይዞ መነሳት አለበት። ዛሬ ታሪክ የሚሰራበት ወቅት ላይ በመሆናችን ሁላችንም በየተሰለፍንበት ሙያ በአንድ ላይ ሆነን ወደ አምላካችን በመጸለይ እና ጠንክሮ በመታገል ዘረኝነትን ለማጥፋት፣ የሃገራችንን አንድነት ለማስከበር ባጠቃላይ ኢትዮጵያ በምድሯ ላይ የሚኖሩ ዜጎቿ ሁሉ በሰላም፣ በአንድነት እና በፍቅር የሚኖሩባት ሃገር ትሆን ዘንድ ሁላችንም የድርሻችንን እንወጣ።

በመጨረሻም በመጽሃፍ ቅዱስ ላይ እንደምናነበው ነቢየ ነቢያት ቅዱስ ዳዊት እድሜ ዘመኑን ሁሉ ለሃገሩ፣ ለህዝቡና ለሃይማኖቱ ሲል ከጠላቶቹ ጋር እንደተዋጋና በእግዚአብሄር ቸርነት በጠላቶቹ ላይ ድልን እንደተቀዳጀ እንረዳለን። ቅድስት ሃገር ኢትዮጵያ እየጠፋች እጃችንን አጣጥፈን በመቀመጥ ከእግዚአብሄር ብቻ ለውጥ መጠበቅ ፈጣሪን መፈታተን ነው። እግዚአብሄር አስተዋይ አይምሮና ሙሉ የሰውነት ክፍል ሰቶናል በመሆኑም ሁላችንም እንደ እንደ ቅዱስ ዳዊት ለሃገራች፣ ለሃይማኖታችን እና ለህዝባችን በመቆም ሃገረ አትዮጵያን እንታደጋት።

## የወያኔ ጀሃዳዊ ሀረካት ድራማ የሙስሊሙን ማህበረሰብ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ከመንግስት ካዝና በወጣ ገንዘብ የተሰራ ፊልም ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የስልጣን ዘመኔን ያራዝምልኛል ብሎ ካመነ ምንም ነገር ከማድረግ እንደማይመለስ በግልፅ ያሳያል ብለዋል።

ባለፉት ሃያ አንድ አመታት ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ጠንክሮ የተቃወማቸዉንና ህዝብ የሚወዳቸዉን ድርጅቶችና ግለሰቦች “ህገመንግስት አፍራሽ” ወይም “ሽብርተኛ” የሚል ስም በመለጠፍ ፊልምና ድራማ እየሰሩ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማታለል መሞከራቸዉ የሚታወስ ነዉ። ህዝብ በሠላማዊ መንገድ የሚያቀርብለትን ጥያቄ በአግባቡ ከመመለስ ይልቅ ህዝብን መደፍጠጥ የሚቀናዉ ወያኔ ከሰሞኑ “ጂሀዳዊ ሀረካት” የሚባል ፊልም አቀነባብሮ ለህዝብ ያቀረበዉ ላለፉት 12 ወራት ሽንጣቸዉን ገትረዉ የታገሉትን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለማሰር፤ለመደብደብና ለመግደል የሚያስችል ይሁንታ ከኢትዮጵያ ህዝብና ከአለም አቀፉ ህብረተሰብ የሚያስገኝለት መስሎት ነዉ።

የፊልሙን ይዘትና ቅርጽ አስመልክቶ የዝግጅት ክፍላችን በስልክ ያናገራቸዉ በርካታ ኢትዮጵያውያን የወያኔ አገዛዝ ክርስቲያኑንና ሙስሊሙን በማጣላት በአንድ በኩል የክርስቲያኑን ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት ሙከራ እያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱን የሐይማኖት ህብረተሰቦች በማጣላት ህዝብ ለመብቱና ለነጻነቱ በሚያደርገዉን ትግል ላይ ዉኃ ለማፍሰስ የሚያርገዉ ከንቱ ሙከራ እንደሆነ ገልጸዋል። አንድ ስማቸዉ እንዳይገለጽ የጠየቁን የእስልምና እምነት ተከታይ የኢትዮጵያ ህዝብ ጨዋና አዋቂ በመሆኑ በወያኔ ፕሮፓጋንዳ ተታልሎ እርስ በርሱ አይጋጭም ካሉ በኋላ ይህንን ርካሽ የወያኔ ፕሮፓጋንዳና የዉሸት ማስጠንቀቂያ ሙስሊሙ ህብረተሰብ አይሰማዉም ክርስቲያኑም ቢሆን በጭራሽ አይቀበለዉም ብለዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢቲቪ ያስተላለፈውን ውሳኔ በመቃወም”ይድረስ ለሁሉም” የሚልና በኢቲቪ የተላላፈዉን የወያኔ ድራማ የሚኮንኑ የኤስ ኤም ኤስ መልእክቶች በመላ አገሪቱ ተሰራጭተዋል።

ለየት ባለ ዜና ደግሞ በእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ ከተሰራዉ ድራማ ጋር ተመሳሳይነት ያለዉና ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስን፤ ብጹዕ አቡነ መልክአ ጻዲቅንና ብፁዕ አቡነ መቃሪዎስን በሽብርተኝነት የሚፈርጅ ዶክመንተሪ ፊልም ተጠናቅቆ በቅርብ ግዜ ውስጥ ለህዝብ ይቀርባል ተብሎ እየተጠበቀ ነው። ፊልሙ አቡነ መርቆሪዎስን ነፍጥ ካነሱ ሀይሎች በተለይም ከግንቦት ሰባትና ከከአርበኞች ግንባር ጋር ይሰራሉ በሚል የፈጠራ ወንጀል ይወነጅላል። በዚህ በቅርቡ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ይቀርባል ተብሎ በሚጠበቀዉ ድራማ ላይ ወያኔ አጋሮቹ የሆኑትን የሐይማኖት አባቶች በአስረጂነት የሚያቀርብ ሲሆን በዚህ የሀሰት ድራማ ላይ አንሳትፍም ያሉ አባቶች ካሁኑ የወያኔ ጫና መዉጪና መግቢያ እያሳጣቸዉ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

## የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ሦስት ቦታ መከፋፈሉ ተሰማ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባን ሲቆጣር በአምሳያዉ ከፈጠራቸዉ ወያኔ ሰራሽ ድርጅቶች አንዱ የሆነዉ የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ሦስት ቦታ ተከፋፍሎ ለመፍረስ በመንገዳገድ ላይ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኘዉ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ የኦህዴድን ምንጮች ጠቅሶ በላከልን ዜና ገለጸ። ከመለስ ዜናዊ ህልፈት በኋላ በተደረገዉ የስልጣን ክፍፍል ብዛታችንን የሚመጥን ስልጣን አላገኘንም በሚል ከህወሀት ጋርና የህወሀት ደጋፊ ከሆኑ አባላቱ ጋር ከፍተኛ ጭቅጭቅ ዉስጥ ገብቶ የከረመዉ ኦህዴድ ሰሞኑን ለይቶለት ሦስት ቦታ ተከፋፍሎ አገሪቱን ወደ ከፋ የፖለቲካ አዘቅት እየወሰዳት መሆኑ ከየቦታዉ እየተሰማ ነዉ። አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች እምነት ማጣት፣ ሙስናና የግል ጥቅምን ማሳደድ ኦህዴድ ዉስጥ ለሚታየዉ መከፋፈል ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸዉ ብለዉ የሚያምኑ ቢሆንም እንደብዙ የአገር ዉስጥና የምዕራቡ አለም የፖለቲካ ጠበብቶች እምነት ኦህዴድ ዉስጥ ለተፈጠረዉ ችግር ዋናዉ ምክንያት ኢትዮጵያ ዉስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ የኦሮሞ ህዝብ ያለዉ የፖለቲካ ጡንቻ እጅግ በጣም ትንሽ በመሆኑ ነዉ።

ከታማኝ የኦህዴድ ምንጮች በተገኘዉ መረጃ መሠረት በአብዛኛው የኦሮሚያ ዞኖች በተለይም በምስራቅ ኦሮሚያና በአርሲ ዞኖች የሚገኙ የድርጅቱ አባላት ሦስት ቦታ ተከፍለው እርስ በርሳቸዉ እየተነካከሱ ሲሆን እንደ ብዙዎች ግምት ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ 2005 የኦህዴድ መጨረሻ ሊሆን ይችላል እየተባለ በመነገር ላይ ነዉ። በተላይ በዞንና ከዞን በላይ በሆኑ የድርጅቱ አባላት ዉስጥ የሚታየዉ መከፋፋል ዋና ዋናዎቹን የኦህዴድ አመራሮችን መጨመሩንም ለማወቅ ተችሏል። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች እነሱ እንዳሰኛቸዉ የማይቆጣጠሩት ኦህዴድ በሌለበት ቦታ ኢትዮጵያን ተቆጣጥረዉ መኖር እንደማይችሉ በሚገባ ስለሚያዉቁ የኦህዴድን ከፍተኛ የአመራር አባላት በያሉት ግምገማ እንዲያካሄዱ በማስገደድ ላይ መሆናቸዉን ከአገር ቤት የሚደርሱን መረጃዎች ያስረዳሉ።

በኦህዴድና በህወሀት ዉስጥ የሚታየዉን አልበርድ ያለ የርስ በርስ ግጭት እንዲያስረዱን የጠየቅናቸዉ አንድ ምሁር በሰጡን መልስ የኦህዴድና የህወሀት አለመግባባት መነሻዉ አንደኛዉ የነበረኝ ስልጣን ጎደለ የሚል ሌላኛዉ ደግሞ ተናቅን የሚል ስለሆነ እነዚህን የኢትዮጵያን የፖለተካ ስልጣን በተመለከተ ተፃራሪ አቋም ያላቸዉን ድርጅቶች እንደቀድሞዉ በአንድ ግንባር አቅፎ መራመድ አጅግ በጣም አስቸጋሪ ነዉ ብለዋል። እንደምሁሩ አባባል የወያኔ ወይም የኢህአዴግ ዘመን እያለፈ ነዉና ተቀዋሚዎች ይህንን ወርቃማ የሆን ግዜ ተጠቅመዉ ወያኔን ለማስወገድ አብረዉ መስራት አለባቸዉ ብለዋል።

## የወያኔው አምባሳደር ማርቆስ በኒውዚላንድ ከፍተኛ ገጠመው፣ ገንዘብ ለማሰባሰብ ያደረገው ጥረት ያለስኬት ተጠናቀቀ

በኢትዮጵያ የጃፓንና ኦሽያን አካባቢ የወያኔው አገዛዝ ተወካይ የሆነውና መቀመጫውን ቶኪዮ ያደረገው አምባሳደር ማርቆስ ከትናንት በስቲያ እሁድ ከ 2:30 ፒ ኤም ጀምሮ እስከ 6፡00 ፒ ኤም ድረስ ኢትዮጵያዊያኖችን በኒውዚላንድ አክላንድ አሞራ ሆቴል ውስጥ በመሰብሰብ ስለ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ገለጻና ማብራሪያ እስጣለሁ በማለት ጥቂት የሆኑ የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ደጋፊ ግለሰቦች ብቻ አስጠርቶ ለማነጋገር ያደረገው ሙከራ ሳይሳካለት መቅረቱን ዘጋቢያችን ባስተላለፈልን ሪፖርት አመለከተ።

ይህን ዘርን መሰረት ባደረገ ጥሪ በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ቦታው ድረስ በመገኘት አምባሳደሩን በጥያቄዎች ሲያጨናንቁት መስተዋላቸውን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጿል። አምባሳደሩ ወደ ኒውዚላንድ የመጣበት ዋና ምክንያት ከራሱ አንደበት እንደተገለጸው በውጭ ሃገራት የሚገኙት ዲያስፖራ ኢትዮጵያዊያን ወደ ሃገራቸው ገንዘባቸውን በማስገባት ከፍተኛ የሆነ ኢንቨስትመንት እንዲያደርጉ የሚል ሲሆን ለዚህም አገዛዙ አስፈላጊዉን እገዛ ያደርጋል በማለት የተለመደውን የማባበያ ንግግር አድርጓል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት አምባሳደሩ ንግግሩን የጀመረው ለሞተው መለስ ዜናዊ የህሊና ጸሎት እናድርግ በማለት ቢሆንም ይህ ጥያቄው በስብሰባው የተገኙ በርካታ ኢትዮጵያዊያንን ያስቆጣ ከመሆኑም በላይ በሺሆች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ደም ፈሶ የኒህን ኢትዮጵያዊያንን ደም ላፈሰሰ ግለሰብ የህሊና ጸሎት የሚባል ነገር ተቀባይነት የለውም በማለት ጠንካራ ሙግት በማቅረባቸው አምባሳደሩ ሳይወድ በግድ የሊና ጸሎት ተብየውን ለመተውና ወደሚቀጥለው አጀንዳ ማለፍ ግድ ሆኖበታል።

አምባሳደር ማርቆስ ከዘረኛው አገዛዝ የበላይ አለቆቹ የተሰጠውን ትእዛዝና መመሪያ ለመተግበር በርካታ የማባበያ ሃሳቦችን ያቀረበ ቢሆንም በስብሰባው የተሳተፉት ኢትዮጵያዊያን ለማባበያው ምንም ጆሮ ሳይሰጡ ያቀረቧቸው አስተያየትና ትያቄዎች በሙሉ ያተኮሩት በኦትዮጵያ ውስጥ ስላለው የሰ ብ አ ዊ መብት ረገጣና የወያኔ ማለቂያ የለሽ ግፍና በደል፣ እንዲሁም በአስተዳደራዊ መድልኦና በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ ስለሚታየው ዘረኝነት መሆኑ ታውቋል።

በዚሁ ስብሰባ ላይ ከተነሱ ጥያቄዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፣
በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው ችግር የወያኔ እጅ የለበትም በማለት የቅጥፈት ንግግር ላደረገው አምባሳደር ልክ እንዳልሆነና እውነታው የወያኔ እጅ ሙሉ ሙሉ ያለበት ለመሆኑ የራሱ የወያኔ ባለስልጣን የሆነውን ዶር ሽፈራው የተናገረውን ኦዲዮ በማሰማት አምባሳደሩ እንዲሽማቀቅና እንዲያፍር ከማድረጋቸውም በላይ ለዚህ እውነታ አምባሳደር ማርቆስ የሰጠው መልስ ሌላና እንዲህ አይነት ነገር አልሰማሁም መረጃም የለኝም የሚል ተጨማሪ ነጭ ውሸትን ነበር።

ኢትዮጵያዊያኑ በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ እየተከተለ ያለው የውሻው ይጩህ ግመሉ ይሄዳል አባባል ፍጹም ትክክል እንዳልሆነና አንድ ቀን የሚጮከው ውሻ እንደሚናከስም ሊታወቅ ይገባል በማለት ሃይለማሪያም ደሳለኝ ለሰላም ድርድር አስመራ እሄዳለሁ ሲል ለምን ከሃገር ውስጥ ተቃዋሚዎች ጋር የሰላም ድርድር ማድረግ አልታሰብ አለው ብለዋል።

አንዲት እድሜዋ በሃያዎቹ ውስጥ የምትገመት ወጣት ተነስታ አምባሳደር አንተ ስለ ቴረሪስት ስታወራ ሰማሁህ፣ ለመሆኑ ይህ ቴረሪስት የሚለው ቃል ፍቺው ባንተ እይታ እንዴት ነው? የቴረሪስት ድርጊትስ ምንድነው? ለምሳሌ እኔ ወድዚህ አዳራሽ ስገባ ቼክ ልታደርገኝ ፈለግህ ፣ እኔም በሙስሊም ባህል ወንድ ሴትን እንደማይፈትሽ ነገርኩህ፣ ነገር ግን ይህ ድርጊቴ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን ኖሮ እራሴን የማገኘው እስር ቤት ነበር። እናም ፍቺውን ንገረኝ ብላ አፋጥጣዋለች።

በመጨረሻም ለአምባሳደሩ የተላለፈለት መልእክት ይህ ስልጣን የተሰጠህ ከምድራዊው የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ነው። ኢትዮጵያና ህዝቧ እንዲህ ሲሰቃዩ እያየህና እየሰማህ እንዳላየህና እንዳልሰማህ መሆንን ለህሊናህ ትተነዋል። ይህን ስልጣን ይዘህ ህዝብን መበደል ወይንም ወደ ህሊናህ ተመልሰህ ከህዝብ ጋር መሆን ምርጫው ያንተ ነው የሚል እንደ ነበር ዘጋቢያችን ገልጿል።

## ከፋፋዩ የወያኔ አገዛዝ ህዝብን ከመሪዎቹ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የታየ ከመሆኑም በላይ እጂግ በርካታ ሙስሊሞችም ክልብ በሆነ ምሬት ለ አምላካቸው ሲነግሩና ሲያለቅሱም እንደነበር ታውቁአል።

ዘጋቢያችን በዚሁ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የተገኙ አንዳንድ ሙስሊሞችን በማነጋገር የላከልን ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ የወያኔ አገዛዝ ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን መብታችንን ለማስከበር እያደርግን ያለነውን ቁርጠኛ ትግል ከመጤፍ ካለምቁጠሩም በላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚወስደውን ርምጃ የከፋ እያደረገና የርስ በርስ እልቂት እንዲፈጠርም ግፊት እያደረገ ነው ብለዋል። የወያኔ አገዛዝ ሙስሊሙን ህብረተሰብ ከአመራር ኮሚቴዎቹ ለመነጠል አስቀያሚ ተንኮል ቢጠነሥም ይህ የተፈበረከ ድራማው የአገዛዙን ብልግናና ተራነት ከማጋለጥ አልፎ እንዲያውም ሙስሊሙ ህብረተሰብ በተቃራኒው ለአመራር ለኮሚቴ አባላቱ ያለውን ፍቅርና ክብር እንዲጨምር ማድረጉን ገልጸዋል። እነኝሁ አስተያየት ሰጪዎች ወያኔ እንኩአን እንዲህ አይነት ድራማ ይቅርና በህይወታችንም ላይ ርምጃ ለመውሰድ ቢመጣ በምንም መልኩ ግምባራችንን አናጥፍም ካሉ በሁአላ ትግላቸው ለጥያቄአቸው ምልስ ሰስከሚያገኙ ድረስ እንደሚቀጥልና ለዚህም ምንም ጥርጥር እንደኢለላቸው ገልጸዋል።

እነኝሁ ኤትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በዚሁ የተቃውሞ ሰልፍ ሲያሰሙ ከነበሩአቸው መፈክሮች መካከል እኛ አቡበከር ነን፣ እኛ ያሲን ነን እኛ ኮሚቴውን ነን፣ እኛ ካሚል ሸምሱን ነን፣ ኢ ቲ ቪ ውሸታም፣ መሪዎቻችን ይፈቱ ና ሌሎችም የጠሩአቸው የኮሚቴ አባላቶች ስም ይገኝበታል።

ይህ በንዲህ እያለ የተቃውሞ ሰልፉ እየተጠናቀቀ ይገኝ በነበረበት ወቅት መርዘኛ የሆነው የወያኔ አገዛዝ በሰልፈኞቹ መካከል ግጭት እንዲነሳ ለማድረግ ሙከራ ቢያደርግም ሙከራው በኒሁ ጨዋ ሰልፈኞች ብልጠትና ብቃት ሳይሳካለት ቀርቱአል።

ወያኔ ሰልፈኞቹ በቁጣ አዎቶብሶችን እንዲሰብሩ ለመገፋፋት የአንበሳ አውቶብሶች በግድና አስፈሪ ሁኔታ በሰልፈኞች መሃል እንዲገቡና እንዲያልፉ ቢያደርግም ሰልፈኞቹ አንሰብርም፣ አንሰብርም፣ በማለት አውቶብሶቹ በሰላም እንዲያልፉ አድርገዋል። ተንኮለኛ የሆነው አገዛዝ እንደለመደው አግበስብሶ ሰልፈኞችን ወደ እስር ቤት ለማጎር እንዲመቸው በአውቶብስ ላይ ይፈጠራል ብሎ የጠበቀውን ጥቃት ሂደት ለመቅረጽ ከይርጋ ሃይሌ ህንጻ ላይ ቪዲዮ ፊልም ቀራጮች አዘጋጅቶ እንደነበርም ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል።

“ጅሀዳዊ ሀረካት”በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተለቀቀው የፈጠራ ድራማ በሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን በሌሎች እምነት ተከታዮች፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች እና በሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ጭምር ከፍ ያለ ተቃውሞና ውግዘት እየቀረበበት ይገኛል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፡- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>፡- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org